# በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
# የኢንፎርሜሽንና ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
## የሚዘጋጅ ወርሃዊ ዲጂታል መጽሔት

**ህዳር/2018 ዓ.ም**




### ማውጫ

የማዕድን ኤክስፖ ም/ጠቅላይ ሚኒስት-————1
2ኛው የኢትዮ ሳዑዲ የጋራ ንግድ ምክር ቤት—--1
የኢትዮ-ሳዑዲ ቢዝነስ ፎረም ————————-2
የኢትዮጵያ እና ስዊድን B2B————————2
የማሌዥያ ጠቅላይ ሚኒስትር ———————3
የማሌዥያ ጠቅላይ ሚኒስትር የአቶ ሰብስብ———3
ለሳኡዲ የልዑካን ቡድን የክብር ስጦታ——-——4
ሃገር አቀፍ የቡና ዕውቅና ም/ጠ/ሚኒስትር——5
የኢትዮጵያና የቱርክዬ ውይይት—-—————5
የአቶ ሰብስብ መልዕክት ስለ ቡና ሽልማት———-6
በሁከት እና በሚድያ ጋጋታ ————————7
የቦርድ አባላትና ክልሎች በማዕድን ውይይት—-7
የስዊድን ኤምባሲ ——————————8
የዴንማርክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ——————-8
የኢትዮጵያ አዘርባጃን ቢዝነስ ፎረም —————-9
የኢትዮጵያ አዘርባጃን ቢዝነስ ፎረም —————-9
ከቻይና ኩባንያዎች ጋር ውይይት——————10
ከአቶ አዲሱ አረጋ ጋር ውይይት———————11
የአቶ ሰብስብ ጉብኝት በቢሾፍቱ——————-11
የኢትዮ ባንግላዴሽ ቢዝነስ ፎረም——————12
የቦርድ አባላት ስልጠና በቦንጋ ከተማ—————-12
ዶክተር ዓይናለም ከቻይና ልዑካን ጋር—————13
አቶ ጸደቀ ከቱርኪየ ኩባንያ ጋር ውይይት———13
ዶክተር ቀነኒሳ ከቡና ቆይዎች ማህበር ጋር——-14
ዶክተር ቀነኒሳ ከጎበዝ ኤሌክትሪክ አምራች——14
ከአሜሪካ ቻምበር ጋር ውይይት———————-15
ለቦርድ ስልጠና በቤንሻንጉል———————-16
ፕሬዚዳንቱ ስለ AFCFTA ስልጠና——————-16
የTVET ማስተባበሪያ ማዕከል መከፈት————17
የGlobal Female ወርክሾፕ———————-17
የጥራት መንደር ምን ይዟል———————-18
አድራሻ——-——————————20

**በኢትዮጵያ የማዕድን ዘርፍ ኢንቨስት ያድርጉ በሚል መሪ 4ኛዉ አለም አቀፍ የማዕድን ኤክስፖ በአዲስ አበባ ኮንቬንሽን ማዕከል በኢፌዲሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ ተከፍቷል።**







የአገራችን የግሉ ዘርፍ ድምፅና ተወካይ የሆነዉ የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድ እና የስራ አመራር አባላትም በኤክስፖዉ ላይ ተሳትፈዋል።

ከአባል ምክር ቤቶችም የኦሮሚያ የሲዳማ የደቡብ ኢትዮጵያ የሱማሌ የሐረሪ እንዲሁም የአዲስ አበባና የድሬደዋ ከተማ አስተዳር የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንቶች ተካፍለዋል። ኤክስፖዉን በንግግር የከፈቱት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ ኢትዮጵያ በተለያዩ የማዕድን ሀብት የታደለች አገር ብትሆንም እስከዛሬ ድረስ ከዘርፉ ያገኘችዉ ጥቅም በቂ እንዳልሆነ ጠቁመዉ አሁን ግን የአገር ዉስጥና የዉጭ የግሉ ዘርፍ አንቀሳቃሾችን በማሳተፍ ዘርፉን ለማልማት ምቹ ሁኔታዎች መፈጠራቸዉን አስረድተዋል።

**ሁለተኛው የኢትዮ ሳዑዲ የጋራ ንግድ ምክር ቤት ስብሰባ ዛሬ በአዲስ አበባ ራዲሰን ብሉ ሆቴል ተካሂዷል፡፡**







የጋራ ምክር ቤቱ ስብሰባ መጀመርያ ላይ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ንግድ የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስብ አባፍራ አባጆቢር በኢትዮ-ሳዑዲ የጋራ ንግድ ምክር ቤት ማዕቀፍ መሰባሰብ ለሁለቱ አገሮች ትልቅ ዕድል መሆኑን በመግለፅ የጋራ ምክር ቤቱ በሁለቱ አገሮች መካከል ጠንካራ የውይይት፣ የትብብርና አጋርነት መድረክ ሆኖ የሚቀጥል ነው ብለዋል፡፡

ይህ በኢትዮጵያ የተካሄደው ሁለተኛ የጋራ የንግድ ምክር ቤቱ ስበሰባም የቀጣይ ትብብራችን አካል ነው ያሉት አቶ ሰብስብ በሁለቱ አገራት የንግድ ማህበረሰቦች መካከል ያለውን ጥልቅ ግንኙነት ከሚያንፀባርቁ በርካታ መድረኮች አንዱም ነው ብለዋል፡፡





የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልና የኢትዮ-ሳዑዲ ያጋራ ንግድ ምክር ቤት የኢትዮጵያ ሰብሳቢ መጋቢ ስርዓት ታዬ ለታ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር ይህ የጋራ ምክር ቤት መቋቋሙ በኢትዮጵያና በሳዑዲ አረቢያ መካከል ቀጣይነት ያለው ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ለምናደርገው ጥረት እንደ አንድ ጠንካራ እርምጃ የሚወሰድ ነው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን የንግድ ግንኙነት ለማጠናከር ያለውን ቁርጠኝነት የገለፁት መጋቢ ታዬ የትዮጵያና የሳዑዲ ኢንተርፕራይዞች ትርጉም ያለው ውይይት እንዲያደርጉ፣ የገበያ መረጃ እንዲለዋወጡና የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያመጡ ስራዎችን እንዲያዳብሩ እንደሚያስችላቸውም አስረድተዋል፡፡

በሳዑዲ አረቢያ የጋራ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ የሆኑት አብዱላህ አልአጂሚ በበኩላቸው በሁለቱ አገራት መካከል የጋራ ምክር ቤት መቋቋሙ የመንግስቶቻችንን የጋራ ራዕይ ወደ ተግባራዊ የኢኮኖሚ ውጤቶች በመተርጎም ስራን የሚፈጥር፣ ዕድገትን የሚያነቃቃና የንግድ ፍሰቶችን የሚያጎለብት ነው ብለዋል፡፡

በውይይት መድረኩ ላይ በሳዑዲ አረቢያ የኢትዮጵያ አምባሳደር የሆኑት አምባሳደር ዶ/ር ሙክታር ከድርም የተሳተፉ ሲሆን አሁን ላይ የኢትዮጵያ መንግስት ካደረገው የኢኮኖሚ ሪፎርሞች ጋር ተያይዞ በርካታ የሳዑዲ ባለሀብቶችን ሊያሳትፉ የሚችሉ ዘርፎች መኖራቸውን በኢትዮጵያ በኩል የተገለፀላቸው ሲሆን ከሳዑዲ የመጡ የጋራ ምክር ቤቱ አባላትም የሳዑዲ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማረግ ፍላጎት እንዳለቸው አስረድተዋል፡፡

## የኢትዮ-ሳዑዲ ቢዝነስ ፎረም በአዲስ አበባ ማሪዮት ሆቴል ተካሄደ።

**አገሪቷ ያላት የኢንቨስትመንት አማራጮች ምቹ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች የኢትዮጵያ ጂኦ ፖለቲካዊ መገኛ ለመካከለኛዉ ምስራቅ አገሮች ወደ አፍሪካ ገበያ ለመግባት ምቹ መሆኑ እንዲሁም አምራች የሰዉ ኃዮል አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት መኖሩ በመንግስት ከፍተኛ ኃላፊዎች ተገልጿል።**







‹‹ኢትዮጵያና ሳውዲ አረቢያ በዲፕሎማሲና በህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ጠንካራ ወዳጅነት ያላቸው አገራት  መሆናቸውን አቶ ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ፕሪዚዳነቱ ይህንን ያሉት ዛሬ በአዲስ አበባ ማሪዮት ሆቴል በተካሄደው የኢትዮ- ሳዑዲ የቢዝነስ ፎረም ላይ ባደረጉት ንግግር ነው፡፡





ለአመታት የቆየው የሁለቱ አገራት ግንኙነትም በንግድ፤ በኢንቨስትመንት፣ በኢንዱስትሪ እና በቱሪዝም ዘርፎችም ከጊዜ ወደጊዜ የበለጠ እየተጠናከረ የመጣ መሆኑንም አቶ ሰብስብ አስረድተዋል፡፡ በንግድና ኢንቨስትመንት መስኮች የሁለቱን አገራት ግንኙነት የበለጠ ወደ አዲስ ምዕራፍ ለማሸጋገር እንዲረዳ፤ የአገራቱ የንግድ ምክር ቤቶች የጋራ የንግድ ካውንስል የመሰረቱ ሲሆን፤ ዓላማውም ሁለቱም አገራት የንግድ መረጃ ልውውጥን እንዲያጎለብቱ፤ የኢንቨስትመንት አማራጮችና ዕድሎች የሁለቱን አገራት ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ እንዲጠቀሙ ለማገዝ፣ የስራ ፈጠራን ሊያበረታቱ እና ምርቶችን እና አገልግሎቶችን ሊያስተዋውቁ የሚችሉ ኤግዚቢሽኖችን በጋራ ለማካሄድ እንዲሁም ንግድ ለንግድ ውይይቶች የሚጠናከሩበትን መደላድል ለመፍጠር ነው ብለዋል አቶ ሰብስብ።

ኢትዮጵያ ለንግድና ኢንቨስትመንት ምቹ የሆኑ መልካም ዕድሎች ያላት አገር እና ልዩ የመልማት አቅም ፣ ሰፊ እና የሰለጠነ የሰው ኃይል፤ ምቹ የህግ ማዕቀፍ እንዲሁም በመንግስት በኩል አስፈላጊ የሆኑ የድጋፍ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን በመግለጽ፣  የሳዑዲ አረቢያ ባለሃብቶችም ይህንን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም  በግል ወይም በጋራ ከኢትዮጵያ ባለሃብቶች ጋር ማልማት እንዲችሉም ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

**የኢትዮጵያ እና ስዊድን የቢዝነስ ለቢዝነስ ውይይት ( B2B) በአዲስ አበባ ሸራተን አዲስ ሆቴል ተካሄደ።**







በውይይቱም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ጸደቀ ድጋፌ፣ የስዊድን የምሥራቅ አፍሪካ የንግድ ምክር ቤት ሊቀመንበር ጆአኪም ዳቪድሠን እንዲሁም የኢትዮጵያ እና ስዊድን ኩባንያዎች ተገኝተዋል።

የሁለቱ ሀገራት ቢዝነስ ልውውጥ ወደ ተሻለ ደረጃ ከፍ እንዲል አበርክቶ ይኖረዋል ተብሏል። የስዊድን ኩባንያዎች በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ፣ በታዳሽ ሀይል፣ በመልሶ መጠቀምና በሌሎችም የማምረቻ መሥኮች የተሻለ አቅም ያላቸው ሲሆን ከኢትዮጵያ አቻዎቻቸው ጋር በትብብር መሥራት እንደሚፈልጉ ጆአኪም ዳቪድሠን ገልጸዋል።  የስዊድን የምሥራቅ አፍሪካ የንግድ ምክር ቤት እንደ ሌሎች የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት በኢትዮጵያም የመሥራት ፍላጎት እንዳለው ተጠቁሟል።

**የማሌዥያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዳቶ ሴሪ አንዋር ኢብራሂም በኢትዮጵያ ቆይታ  እያደረጉ ነው።**




በውሏቸውም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤትን ጨምሮ የተለያዩ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ተወካዮች በተገኙበት በሁለቱ አገራት ባለው ወዳጅነትና ትብብር  እንዲሁም በንግድና ኢንቨስትመንት ዙሪያ መክረዋል።

በመድረኩም ክቡር የኢፌዴሪ ፕሬዘዳንት አምባሳደር ታዬ አፅቀስላሴና  የንግድና ቀጣናዊ ሚኒስትሩ ዶክተር ካሳሁን ጎፌም ተገኝተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ትላንት አዲስ አበባ ሲገቡ ክቡር  ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል።

**ክቡር የማሌዢያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዳቶ ሴሪ አንዋር ኢብራሂም የተመራ ልዑክና ክቡር ፕሬዚደንት ታዬ አጽቀስላሴ በተገኙበት የቢዝነስ ፎረም ላይ ተገኝቻለው።**






የሁለቱ ሃገራት ግንኙነት በሰፊ መሰረት ላይ እያደገ ያለ ሲሆን በተለይ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን አብይ አህመድ (ዶ/ር) ባለፈው ዓመት ጥቅምት ወር ማሌዢያን ከጎበኙ ወዲህ በሁለትዮሽ የንግድ ግንኙነትና የኢኮኖሚ ትብብር አዲስ ምዕራፍ ተከፍቷል። በማሌዢያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዳቶ ሴሪ አንዋር ኢብራሂም ዛሬ ስለ ኢትዮጵያ ቀደምት ታሪክ በሰፊው መነሳቱ ለዛሬው የሁለቱ አገራት የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እና የህዝብ ለሕዝብ ግንኙነት የማይዘጋ በር ይከፍታል :: ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የሁለቱን አገራት የንግድ ግንኙነት እና ኢንቨስትመንት ለማጠናከር ከአቻው ከማሌዢያ ንግድ ምክር ቤት ጋር እየሰራ መሆኑ ይታወቃል::

ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት  ፕሬዚደንት

Har’a waltajjii daldalaa Kabajamoo Ministira Muummee Maaleeziyaa Daato’ Seri Anwar Ibraahim, fi Kabajamoo Pirezidaantii Itiyoophiyaa Taayyee Atsekesalaasiin durfamu irratti as jira. Hariiroon biyyoota lamaanii bu’uura bal’aa ta’een guddachaa kan jiru yoo ta’u, keessumattuu erga Kabajamoo Ministira Muummee keenya Abiy Ahmad (Dr.) bara darbe Onkoloolessa keessa Maaleeziyaa daawwatanii booda hariiroo daldalaa biyyoota lamaanii fi tumsa diinagdee irratti boqonnaan haaraan banamee jira. Muummichi ministeeraa Dato’ Seri Anwar Ibraahim har’a waa’ee seenaa Ityoophiyaa ganamaa dubbachuun isaanii hariiroo diinagdee, siyaasaa fi ummataa biyyoota lamaan gidduu jiruuf balbala bana. ::

Akkuma kanaan dura gabaafame, Manni Maree Daldalaa fi Industirii Itiyoophiyaa gita isaa Mana Maree Daldalaa Maaleeziyaa waliin ta’uun hariiroo daldalaa fi invastimantii biyyoota lamaanii cimsuuf hojjechaa jira.

### የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ለሳኡዲ የልዑካን ቡድን የክብር ስጦታ አበርክቷል።
























**ክቡር ምክትል ጠቅላይ ሚንስትር እና የዕለቱ የክብር እንግዳ አቶ ተመስገን ጥሩነህ በተገኙበት "ፈጠራ እና ፍጥነት ለቡናችን ስኬት" በሚል መሪ ቃል በተዘጋጀው የ2018 ሃገር አቀፍ የቡና ዕውቅና መርሃ ግብር ተካሄዷል ::**








ቡና ለአገራችን የውጭ ምንዛሬ ግኝት ለዘመናት የአንበሳውን ሚና እየተጫወተ የሚገኝ ሲሆን በ2017 በጀት ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ 2.65 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቶበታል:: በዛሬው መድረክም የላቀ ውጤት እና አስተዋጽኦ ላበረከቱ የቡና ላኪዎችና ባለድርሻ አካላት እውቅና መስጠቱ፣ መልካም ተሞክሮዎችን ለማስፋፋትና ሌሎችን በማትጋት በቀጣይ ከዚህ ዘርፍ የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ የሚያስችል እንደሚሆን እምነት ተጥሎበታል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር

Har'a Sagantaan Beekamtii Buna Biyyaalessaa bara 2018 mata duree "Kalaqaa fi Saffisa Milkaa'ina Buna Keenyaaf" jedhuun bakka Kabajamoo Itti Aanaa Muummee Ministeeraa fi Keessummaan Kabajaa Guyyaa kanaa obbo Temesgen Tiruneh argamanitti gaggeeffameera. Bunni jaarraa hedduuf sharafa alaa biyya keenyaaf argamsiisuu keessatti gahee olaanaa taphachaa kan ture yoo ta'u, bara baajataa 2017tti yeroo jalqabaatiif doolaara biiliyoona 2.65 ol era argameera. Waltajjii har'aa irratti al-ergitoota bunaa fi qooda fudhattoota bu'aa fi gumaacha olaanaa galmeessaniif beekamtii kennuun muuxannoowwan gaggaarii babal'isuu fi gara fuula duraatti damee kanaan bu'aa guddaa akka galmeessan namoota biroo kakaasuuf akka gargaaru ni amanama.





**የኢትዮጵያና የቱርክዬ የግሉ ዘርፍ ተወካዮች በአዲስ አበባ ራዲሰን ብሉ ሆቴል የጠረጴዛ ዙርያ ዉይይት አካሂደዋል።**

በጠረጴዛ ዙርያ የምክክር መድረኩ ላይ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) የኢትዮጵያ የግሉ ዘርፍ የሆነዉ አገር አቀፉ የንግና







ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከሐምሌ 2016 ጀምሮ እራሱን በአዲስ መልክ በማደራጀት የተቋቋመለትና ዓላማ ለማሳካት ከምንጊዜዉም በተሻለ ሁኔታ እየሰራ መሆኑን ለልዑካን ቡድኑ አስረድተዋል።

ኢትዮጵያና ቱርክ የቆየ ጠንካራ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር እንዳላቸዉ ያነሱት ዋና ፀሐፊዉ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያ መንግስት ተግባራዊ ያደረገዉ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያ ለዉጭ ባለሀብቶች ተዘግተዉ የቆዩ የኢንቨስትመንት መስኮች መከፈታቸዉ ለቱርክዬ ባለሀብቶችም መልካም አጋጣሚ መሆኑን በማስረዳት በኢትዮጵያ ኢንቨስት እንዲያደርጉ






ጥሪያቸዉን አቅርበዋል። በዉይይት መድረኩ ከ25 በላይ በሚሆኑት የኢትዮጵያና የቱርክዬ ባለሀብቶች መካከል የአቻ ለአቻ የቢዝነስ ምክክሮችም ተካሂደዋል።



“ቡናን ወደ ውጭ በመላክ የላቀ ውጤት ላስመዘገባችሁና አስተዋፅኦ ላበረከታችሁ ቡና ላኪዎችና ባለድርሻ አካላት በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር አቶ ተመስገን ጥሩነህ እውቅናና ሽልማት ስለተበረከተላችሁ የተሰማኝን ደስታ እየገለፅኩ እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት እወዳለሁ። በ2017 ዓ.ም ቡናን ወደ ውጭ በመላክ የተገኘውን የ2.65 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በ2018 ዓ.ም ከ3 ቢሊዮን ዶላር በላይ ለማድረስ የተያዘውን ዕቅድም በጋራ እናሳካለን!

I WOULD LIKE TO EXPRESS MY HAPPINESS AND CONGRATULATIONS TO THE COFFEE EXPORTERS AND STAKEHOLDERS FOR YOUR OUTSTANDING ACHIEVEMENTS AND CONTRIBUTIONS IN EXPORTING COFFEE, FOR BEING RECOGNIZED AND AWARDED BY DEPUTY PRIME MINISTER, HIS EXCELLENCY ATO TEMESGEN TIRUNEH. TOGETHER, WE WILL ACHIEVE THE GOAL OF INCREASING THE FOREIGN EXCHANGE EARNINGS FROM COFFEE EXPORTS FROM 2.65 BILLION US DOLLARS IN 2024/25 TO MORE THAN 3 BILLION US DOLLARS IN 2025/26.”

**ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር**
**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት**






**“ፈጠራ እና ፍጥነት ለቡናችን ስኬት”**

**በሁከት እና በሚድያ ጋጋታ ፍትህም ታሪክም ልማትም አይቀለበስም!**

**ንጉስ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ምን አሉ?** እኛ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ንግድ ለሕዝባችን የሀብት ማበልጸጊያ፤ ለአገራችን የኢኮኖሚ እድገት መሰረት መሆኑን ተገንዝበን፤ የንግድ ፣ የኢንዱስትሪና የእርሻ ሥራ በንጉሠ ነገሥት መንግስት ግዛታችን እንዲስፋፋና፤ ያገራችንም ኢኮኖሚ እንዲዳብር ይረዳል፡ ብለን በማመን ነጋዴዎችም ተሰማሚ የሆነ የተለያ መሰብሰቢያና መተባበሪያ ሥፍራ እንዲኖራቸው አስበን በ34 ኛው ዘመነ መንግስታችን ይህንን የኢትዮጵያን ንግድ ምክር ቤት ሕንፃ መርቀን ከፍተናል።


LAND HOLDING RIGHTS CERTIFICATE
CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA
Landholding Registration and Information Agency
Kirkos SUB CITY OFFICE
Right Holders Description
Parcel Description






የካቲት 23 ቀን 1957 ዓም እኛም ዛሬ ላይ ቆመን እንላለን እናመሰግናለን!

በሁከት እና በሚድያ ጋጋታ ፍትህን ታሪክን ልማትን መቀልበስ አይቻልም። የንጉሡን ቃል እና ሕንጻው ያረፈበት ካርታን እንዲሁም የአሁኑን ገፅታ አያይዘናል ፡፡

Seenaas ta'e misoomni jeequmsaa fi miidiyaadhaan ololaan duubatti deebi'uu hin danda'u! Mootiin Hayile Sillaasee I maal jedhe? Nuti Jaalatamtuu Haayilasillaasee 1ffaa, Emperor Itophiyaa Waaqayyoon sodaatu, . Daldalli ummata keenyaaf madda qabeenya ta'uu isaa hubachuun; bu'uura guddina dinagdee biyya keenyaa; daldalli, industirii fi qonnaan diinagdeen biyya keenyaa akka babal'atu fi guddatu ni gargaara jedhanii amanuudhaan; akkasumas kun daldaltoonni bakka itti walga'anii fi tumsan akka ta'u amanuudhaan gamoo Mana Maree Daldalaa Itoophiyaa kana bara bulchiinsa keenya waggaa 34ffaatti eebbifneerra. Bitootessa 23, 1957 Dh.K.D Har'a as dhaabannee jenna Galatoomaa!!!!! Jeequmsaa fi miidiyaan ololaan seenaa fi misooma duubatti deebisuu hin dandeenyu. Dubbii mootichaa fi kaartaa bakka gamoon kun itti argamu, akkasumas bifa isaa yeroo ammaa woliti qabsiifneera.

**የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባለትና የክልሎች እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች ፕሬዚዳንቶች በኢትዮጵያ የማዕድን ልማት ዘርፍ ባሉ ዕድሎች ምቹ ሁኔታዎችና የፖሊሲ ድጋፎች ዙርያ ተወያዩ።**






በዉይይቱ ላይ በከገሪቱ ስላሉ የማዕድን ሀብት ክምችትና ስርጭት እንዲሁም ስላሉት ዕድሎች የመነሻ ፅሑፍ ያቀረቡት በማዕድን ሚኒስቴር የማዕድን ግብይት የስራ ኃላፊ ዶ/ር እዮብ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የማዕድን ሀብት ክምችት ያላትና አሁን ላይ የማልማት ምቹ ሁኔታዎች መፈጠራቸዉን አስረድተዋል።





**የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ቀነኒሳ ለሚ (ዶክትሬት፣ ተባባሪ ፕሮፌሰር)፣ አዲስ አበባ በሚገኘው የስዊድን ኤምባሲ የግሉ ዘርፍ ልማትና የገበያ ሥርዓት ሁለተኛ ጸሐፊ ከወይዘሮ ኒኮላ ኤሪክሰን ፋኬ ጋር ተወያይተዋል።**

**ዋና ጸሃፊው ስለ ምክር ቤቱ ስራዎች እና ስለተደረገው ተቋማዊ የሪፎርም ስራዎች ላይ ተወያይተዋል። የስዊድን መንግስት ቀደም ሲል በSIDA በኩል ለምክር ቤቱ**






**ሲሰጥ የነበረውን ድጋፍም ጠቅሰዋል።**

**ምክር ቤቱ በቅርቡ ራሱን ያደራጀው ዋና ፀሃፊ እና የግሉን ዘርፍ አቅም መገንባት የሚችሉ በርካታ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ከልማት አጋሮች ጋር እንደሚሰራም ተጠቁሟል፡፡ የስዊድን መንግስት በተለመደው ትብብር የግሉ ዘርፍን የማብቃት ስራውን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ያላቸውን እምነት ገልጸዋል።**

**ወይዘሮ ኒኮላ ኤሪክሰን ፋከል በበኩላቸው የመረጃ ልውውጥን ለማረጋገጥ እና የገንዘብ አቅርቦት በሚኖርበት ጊዜ የወደፊት አጋርነትን ለመወሰን የውይይት መድረኮች ክፍት መሆን አለባቸው ብለዋል።**

**የዴንማርክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቡድን ከኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጋር በፒ 4ጂ መካከለኛ ጊዜ ግምገማ (MTR) ላይ ተወያይቷል።**

የዴንማርክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የለውጥ፣ ትምህርት እና ጥራት ክፍል አማካሪ ሄኔ ካሩስ በምክር ቤቱ የአድቮኬሲና የምርምር ዳይሬክተር ወ/





ሮ ሄለን ረታ ጋር ፕላንና ልማት ሚኒስቴር የሚቆጣጠረውን የኢትዮጵያ የፒ 4ጂ ብሄራዊ መድረክ አተገባበርን አስመልክተው ተነጋግረዋል።

ሁለቱም የመድረኩን ጥንካሬዎች እና ውስንነቶች በአረንጓዴ ልማት እና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት እንዲሁም በአገራዊ የአየር ንብረት ግቦች መሰረት ተወያይተዋል፡፡፡

ወ/ሮ ሄለን የመድረኩን ጥንካሬ እና ውስንነት ገልጸዋል። የP4G ገምጋሚ ቡድን እኤአ ከኖቬምበር 17 እስከ 21 ቀን 2025 በኢትዮጵያ የመስክ ጉብኝት እያደረገ ነው።





እ.ኤ.አ. በ2018 የተመሰረተው የኢትዮጵያ ፒ 4ጂ ብሄራዊ መድረክ ኢትዮጵያን ከአለም አቀፉ ማኅረሰብ ጋር ከሚያገናኘው ከፒ 4ጂ ግሎባል ማዕከል ጋር ግንኙነት እንዲኖር የሚያስችል ነው።

**የኢትዮጵያ አዘርባጃን ቢዝነስ ፎረም በአዲስ አበባ ተካሄደ ።**

በፎረሙም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቢዝነስ ዲፕሎማሲ ዳይሬክተር ጀነራል አምባሣደር ዮሐንስ ፈንታ፣ በኢትዮጵያ የአዘርባጃን አምባሣደር ሩስላን ናሲቦቭ፣ የኢትዮጵያ የንግድና









ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ዓይናለም አባይነህ፣ የሁለቱ ሀገራት የቢዝነስ ተቋማት ተወካዮች ተገኝተዋል። ኢትዮጵያ ለአዘርባጃን ኩባንያዎች ትልቅ የንግድና የኢንቨሥትመንት መዳረሻ መሆን እንደምትችልና ሠፊገበያ ያላት ሀገር ሥትሆን በተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮች መሠማራት እንደሚችሉም ተገልጿል። የአዘርባጃን ኩባንያዎች እንዲሁም የኢትዮጵያ  ነጋዴ ሴቶች ማኅበር አባላትም በፎረሙ ላይ ምርቶቻቸውን ለእይታ አቅርበዋል።







**የኢትዮጵያ አዘርባጃን ቢዝነስ ፎረም የቢዝነስ ለቢዝነስ ውይይት ተካሄደ።**

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቢዝነስ ዲፕሎማሲ ዳይሬክተር ጀነራል አምባሣደር ዮሐንስ ፈንታ፣ በኢትዮጵያ የአዘርባጃን አምባሣደር ሩስላን ናሲቦቭ፣ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ዓይናለም አባይነህ በተገኙበት ፎረም የሁለቱ ሀገራት የቢዝነስ ተቋማት ተወካዮች ተገኝተዋል። በውይይቱም የኢትዮጵያ ሴት ኤክሥፖርተርስ አሶሴሽንና አዲስ ቻምበር ከአዘርባጃን አፍሪካ ኮኦፐሬሽን ጋር የመግባቢያ ሥምምነት ተፈራርመዋል።


በኢሊሌ ሆቴል በተካሄደው ውይይት ኩባንያዎች ምርቶቻቸውን ለእይታ ያቀረቡ ሲሆን የቢዝነስ ለቢዝነስ ውይይት ተካሂዷል። በውይይታቸውም በተለያዩ የቢዝነስ መስኮች ተባብሮ ለመሥራት የተሻለ ልምድ መለዋወጣቸውን ተሣታፊዎች ገልጸዋል።





**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ከቻይና ይው (Yiwu) ከተማ ከተውጣጡ ኩባንያዎች ጋር ተወያዩ።**





ዋና ጸሐፊው ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ በኢትዮጵያ ስለተካሄደው የኢኮኖሚ ሪፎርም፣ በኢንቨስትመንት ምቹ እድሎችና ምክር ቤቱ በሚያከናውናቸው ተግባራት ዙሪያ ገልጸውላቸዋል።

በኢትዮጵያ በተለይም ትኩረት በተሰጣቸው የግብርናና ማምረቻ ኢንዱስትሪ፣ በአይሲቲ፣ በማዕድንና በሌሎችም ዘርፎች በኢትዮጵያ መዋዕለንዋያቸውን እንዲያፈሱና ከኢትዮጵያ ኩባንያዎች ጋር በጋራ እንዲሰሩም ጥሪ አቅርበዋል ዋና ጸሐፊው።





ኩባንያዎቹ በኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች መስራት እንደሚፈልጉም በውይይታቸው አንስተዋል። በማዕከላዊ ዠጂያንግ ግዛት የሚገኘው የቻይናው ይው (Yiwu) በተለይም በጅምላ ንግድ ትልቅ ኢኮኖሚ የሚንቀሳቀስበት አካባቢ ነው። በውይይቱም የምክር ቤቱ ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ጸደቀ ድጋፌን ጨምሮ ሌሎች የስራ ኃላፊዎችና ሰላሳ የሚሆኑ የይው ከተማ ኩባንያዎች ተሳትፈዋል።





**በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር የተመራ የልዑካን ቡድን በቢሾፍቱ የሚገኘውን የካም ሴራሚክ ማምረቻ ፋብሪካን ጎበኘ።**







**የነበረውን ጉብኝት አስመልክቶ ፕሬዚደንቱ እንደገለጹት ኢትዮጵያ በኢንደስትሪው ዘርፍ ያላት ተስፋ የሚያበረታታ መሆኑንና ለስኬቱም ለአምራች ዘርፋ የተሻለ ትኩረት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል::**

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከግብርና ሚንስቴር ጋር ተቀናጅቶ መስራት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ከኢፌዴሪ የግብርና ሚንስትር ክቡር አቶ አዲሱ አረጋ ጋር በፅ/ቤታቸዉ ዉጤታማ ዉይይት አድርገናል ።**






እኔም የምክር ቤቱን ዓላማና ተልዕኮ ለክቡር ሚንስትሩ በዝርዝር አንስቼ የግብርናው ኢንዳስትሪ ዘርፉ፤ ከምክር ቤቱ ጋር ተቀናጅቶ መስራት ለአገር ኢኮኖሚ ግንባታ ያለዉ አዎንታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን እና የምክር ቤታችንን ሚና እና አስተዋፅኦ አስረድቻለው::

ክቡር አቶ አዲሱ አረጋ በበኩላቸዉ በግብርናዉ ክፍለ ኢኮኖሚ ተሰማርተዉ የተለያዩ ምርቶችን በማምረት ላይ የሚገኙ አርሶ አደሮች እሴት ሊጨምሩ ወደሚችሉ ዘርፎች በመሸጋገር ወደ ንግዱም እንዲገቡ ስለምንፈልግ ከምክር ቤቱ ጋር ተቀናጅተን ለመስራትና አስፈላጊዉን እገዛ ለማድረግም ዝግጁ መሆናቸዉን አሳይተውናል።

**ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር**

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት**

**Har'a Ministira Qonnaa Kab. obbo Addisuu Arega, Waajjira isaaniitti, Manni Maree Daldalaa fi Industirii Itiyoophiyaa Ministeera Qonnaa waliin ta'uun hojjechuu akka danda'u erati maryanera.**

**Kaayyoo fi ergama Mana Marichaa Kab. Ministirraaf bal'inaan ibsuun dhiibbaa gaarii dameen indaastirii qonnaa Mana Maree waliin ta'uun hojjechuun guddina dinagdee biyyattii fi barbaachisummaa Mana Maree keenyaa irratti qabu ibseeraaf.**

**Kabajamoo Obbo. Addisuu Aregaa gama isaaniitiin qonnaan bultoonni diinagdee xiqqaa qonnaa irratti bobba'anii fi oomisha oomishaalee adda addaa irratti bobba'an gara damee gatii dabalataatti ce'anii damee daldalaatti akka seenan waan barbaannuuf, Mana Maree waliin tumsaan hojjechuu fi gargaarsa barbaachisaa ta'e kennuudhaaf qophii ta'uu isaanii ibsaniiru.**

## የአፍሪካ- ባንግላዴሽ ቢዝነስ ፎረም በአዲስ አበባ ዲ ሊዮፓል ሆቴል ተካሄደ ፡፡

በዚህ ፎረም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የእስያ፣ መካከለኛው ምሥራቅ እና ፓሥፊክ ሀገራት ጉዳዮች ዳይሬክተር ጀነራል አምባሣደር ደዋኖ ከድር፣ በኢትዮጵያ



የባንግላዴሽ አምባሣደር ኤር ቫይስ ማርሻል ሲትዋት ናየም፣ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ይድነቃቸው ወርቁ፣ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ጸደቀ ድጋፌን ጨምሮ የተለያዩ የመንግሥትና የግል ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም የሁለቱ ሀገራት ኩባንያዎች ተገኝተዋል፡፡

በዝግጅቱም በኢትዮጵያ ሥላለው የኢንቨሥትመንት እድል እና ቢዝነስ ለመሥራት ያለውን ምቹ ሁኔታ የተብራራ ሲሆን ዝግጅቱ የሁለቱን ሀገራት ንግድና ኢንቨሥትመንት ከማሥፋት ባሻገር




ባንግላዴሽን ከአፍሪካ ጋር ለማሥተሣሠር እድል የሚፈጥር መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ የሁለቱ የንግድና ኢንቨሥትመንት ግንኙነት እየተጠናከረ መምጣቱ ሲገለጽ በአሁኑ ወቅት ከስድስት በላይ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ በሥራ ላይ መሆናቸውም ተገልጿል

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከጂ አይ ዜድ ኤዩ ጋር በመተባበር ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትና ከክልሉ ለተዉጣጡ የምክር ቤቱ አመራሮች በአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና መርሆዎች ዕድሎችና ሊያጋጥሙ በሚችሉ ተግዳሮቶች እንዲሁም






ሊደረጉ በሚገቡ ዝግጁነቶች ዙርያ የግንዛቤ መፍጠርያ በቦንጋ ከተማ ስልጠና ሰጠ ፡፡

ስልጠናዉን በንግግር የከፈቱት የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ አገራችን ነፃ የንግድ ቀጠናዉን ለመቀላቀል አስፈላጊዉን ዝግጅት ስታደርግ ቆይታ በዚህ ዓመት መጀመርያ ላይ ምርቶቿን ወደ ኬንያ ደቡብ አፍሪካና ሶማሊያ በመላክ መጀመሯን በይፋ ማብሰሯን በማዉሳት የአገራችን የንግዱ ማህበረሰብ ለዚህ እየገባንበት ላለዉ ብርቱ ፉክክር እራሱን ማዘጋጀት አለበት ብለዋል፡፡





ለዚህ ደግሞ በየደረጃዉ ያሉት የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤቶች የንግዱን ማህበረሰብ የማስገንዘብና የማንቃት ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የቦርድ አባልና የሚዛን ከተማ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ፕሬዚዳንት ወ/ሮ አምሳል ነጋሽ ክልሉ ገና የተመሰረተ እንደመሆኑ መጠን በየደረጃዉ ያሉ የንግድ ም/ቤቶች አመራሮች የሚቻላቸዉን ሁሉ ለማድረግ ጥረት እያደረጉ መሆናቸዉን አስረድተዋል፡፡

## **የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ጸደቀ ድጋፌ ከተርኪዬ ኤሌክትሪካል እና ኤሌክትሮኒክስ ላኪዎች ማኅበር ጋር ተወያዩ።**



የማኅበሩ የቦርድ አባላትና ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ባሉ የኢንቨስትመንት እና ንግድ ምቹ ሁኔታዎች እንዲሁም ከኢትዮጵያ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ አምራች ተቋማት ጋር መስራት በሚችሉባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ተወያይተዋል።

አቶ ጸደቀ ድጋፌ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ባለው ምቹ የኢንቨስትመንት አማራጭ፣ በኤሌክትሪክና በኤሌክሮኒክስ ዘርፍ መስራት በሚችሉባቸው እድሎች ዙሪያ አብራርተውላቸዋል።

የማኅበሩ አባላትም በኢትዮጵያ በኤሌክትሪክና በኤሌክትሮኒክስ በተለይም በኬብል፣ ጀነሬተርና በሌሎችም ዘርፎች ለማምረትና በጋራ ለመስራት ፍላጎት እንዳላቸው ገልጸዋል። በቀጣይ የካቲት ወርም በኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ ዘርፍ የተሰማሩ ኩባንያዎች ወደ ኢትዮጵያ እንደሚመጡና ከኢትዮጵያ አቻዎቻቸው ጋር የቢዝነስ ለቢዝነስ ውይይት ለማካሄድና በትብብር ለመስራት እንደሚፈልጉ አንስተዋል።

የተርኪዬ ኤሌክትሪካል እና ኤሌክትሮኒክስ ላኪዎች ማኅበር  አባላትም የፊታችን ጥር 27-የካቲት 1/2018 ዓ.ም በሚካሄደው 15ኛው ኢትዮ ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢት ላይ እንዲሳተፉ ጥሪ ቀርቦላቸዋል። የተርኪዬ ኤሌክትሪካል እና ኤሌክትሮኒክስ ላኪዎች ማኅበር በኤሌክትሮኒክስ እንዲሁም በኃይል ዘርፍ የሚሰራ ከ4 ሺ በላይ አባላት ያሉት ማኅበር ነው።



Mr. Tsedeke Digafie, Deputy Secretary General of the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA), talks with the Türkiye Electrical and Electronics Exporters Association.

The association's board members and experts discuss possible investment and trade prospects in Ethiopia, as well as options for cooperating with Ethiopian companies working in the electric and electronic sector. The delegation members also expressed the need to work together with their Ethiopian counterparts. Mr. Tsedeke discussed the trade and investment potential open to Türkiye businesses, as well as possibilities for cooperation with Ethiopian companies operating in electric and electronics.



Next February, a delegation from Türkiye Companies will visit Ethiopia for a business meeting with Ethiopian counterparts. Members of the association are also invited to participate in the 15th Ethio Chamber International Trade Fair, which will be held in Addis Ababa from February 4 to 8, 2026. The Türkiye Electrical and Electronics Exporters Association works on electrical-electronics and energy and has 4,000 members across the country.

**የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር አይናለም አባይነህ ከቻይና መንግሥት የልዑካን ቡድን ጋር ተወያይተዋል።**

**ሁለቱ ወገኖች በተለይም የአቅርቦት ሰንሰለት ትብብር፣ ደረጃዎችን ማጠናከር እና የተስማሚነት ምዘና ጉዳዮችን እና ምርቶችን ወደ ውጭ ለመላክ እድል የሚሰጠውን “ትልቅ ገበያ ለሁሉም፡ ወደ ቻይና መላክ” በሚሉ ጉዳዮች ላይ እንዲሁም በሁለቱም ሀገራት የሁለትዮሽ የንግድና የኢንቨስትመንት ዕድሎች ላይ ተወያይተዋል።**






**ዶ/ር ዓይናለም የኢትዮጵያን ወቅታዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያ፣ እምቅ የንግድና ኢንቨስትመንት ተስፋዎች እና ምክር ቤቱ ንግድና ኢንቨስትመንትን በሀገሪቱ ለማበረታታት ያለውን ሚና ተወያይተዋል።**

**የኢትዮጵያን መንግስት እና የግሉ ዘርፍ የሚያስተሳስረው ምክር ቤቱ ለሁለቱም ሀገራት የጋራ ጥቅም ለመስራት ሁሌም ቁርጠኛ መሆኑን አረጋግጠዋል።**

**በኢትዮጵያ የቻይና ኤምባሲ የኢኮኖሚና የንግድ ጉዳዮች ሚኒስትር ሚስተር ሊዩ ዢያኦጓንግ ልዑኩን የመሩት እና በቻይና ያለውን ምቹ ሁኔታ ለኢትዮጵያውያን ቢዝነሶች አብራርተው የቻይና ኩባንያዎች በኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች ለመሰማራት እና ለመስራት ያላቸውን ፍላጎት አብራርተዋል።**

**ለበለጠ የኤክስፖርት ዕድሎች ምርቶችንና አገልግሎቶችን ለማስተዋወቅ ከንግድ ትርዒቶችና ኤክስፖዎች በተጨማሪ የቻይናን የገበያ እድል ለመጠቀምና ወደ ቻይና ኢኒሼቲቭ ለመላክ ሰፊ ገበያ እንዳላት አጽንኦት ሰጥተዋል። ከየካቲት 4 - 8 ቀን 2026 በአዲስ አበባ በሚካሄደው 15ኛው የኢትዮ-ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢት ላይም የቻይና ኩባንያዎች እንዲሳተፉ ምክር ቤቱ ጋብዟል።**

**በውይይቱ ላይ የምክትል ዋና ፀሃፊ አቶ ፀደቀ ዲጋፌ፣ በቻይና ሪፐብሊክ ንግድ ሚኒስቴር የውጭ ንግድ መምሪያ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ሜንግ ዩ እና ሌሎች የሁለቱም ሀገራት የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ተገኝተዋል።**

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ከኢትዮጵያ ቡና ቆይዎችና ፈጭቶ አሻጊዎች የዘርፍ ማህበራት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጋር በጽ/ቤታቸዉ ተወያይተዋል።**





ዋና ፀሐፊዉ የምክር ቤቱን ዋና ዋና ተልዕኮዎችንና በአዋጅ የተሰጡትን ስልጣኖች በዝርዝር ያስረዱ ሲሆን የግሉ ዘርፍ ተሰሚነትን ለማግኘት ተደራጅቶ መንቃሳቀስ ተገቢ ስለሆነ ቡና በመቁላትና ፈጭቶ በማሸግ ዘርፍ የተሰማሩት በዘርፋቸዉ በማህበር መደራጀታቸዉ ይበል የሚያሰኝ ነዉ ብለዋል። የዘርፍ ማህበሩ የበለጠ ለመጠናከርና አስፈላጊዉን ድጋፍ ለማግኘት የአገር አቀፉ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አባል መሆን እንዳለበትም አሳዉቀዋል።

የኢትዮጵያ ቡና ቆይዎችና ፈጭቶ አሻጊዎች የዘርፍ ማህበራት ፕሬዚዳንት አቶ ወንድምአገኝ አለማየሁ በበኩላቸዉ የዘርፍ ማህበሩ በቡና ቆይነትና ፈጭቶ ማሸግ ዘርፍ የተሰማሩ ከ20 በላይ ኩባንያዎችን ይዞ



መመስረቱን ጠቁመዉ ምንም እንኳን የዘርፍ ማህበሩ ህጋዊ እዉቅና አግኝቶ ከተመሠረተ ገና አንድ ዓመቱ ቢሆንም መስራች ኩባንያዎቹ በዘርፉ የበርካታ አመታት ልምድ ያላቸዉ ናቸዉ ብለዋል።

የዘርፍ ማህበሩ ዋነኛ ዓላማም ለዘመናት ወደ ዉጭ እየተላከ ባለዉ አረንጓዴ ቡና ላይ እሴት ጨምሮ መላክ ነዉ ያሉት አቶ ወንድምአገኝ አባላቶቹም ከጥቃቅንና አነስተኛ እስከ ላኪዎች ያሉ መሆናቸዉንም አስረድተዋል።

የዘርፍ ማህበሩ አቅሙን በአግባቡ ለመገንባትና በአገር አቀፍ ደረጃ የተራጁ ነጋዴዎችና አምራቾች የሚያገኙትን ጥቅማጥቅሞች ለማግኘት ከኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጋር ተቀራርቦ ለመስራት እንደሚፈልጉና አመጣጣቸዉም ይህንኑን ግንኙነት ለመፍጠር መሆኑን አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የግሉ ዘርፍ ድምፅና የመንግስትና የግሉ ዘርፍ አገናኝ ድልድይ እንደመሆኑ መጠን አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችን እንደሚሰጣቸዉ ዶ/ር ቀነኒሳ አረጋግጠዉላቸዋል።

## የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ከጎበዝ ኤሌክትሪክ ማኑፋክቸሪንግ ኃ.የተ.የግ.ማ. ዋና ኦፕሬሽን ኦፊሰር አሌክስ ሶንግ ጋር ተውያይተዋል።



**ጎበዝ ኤሌክትሪክ ማኑፋክቸሪንግ ስራውን የጀመረው ከ200 ሚሊዮን ዶላር በሚበልጥ ኢንቨስትመንት ወጭ ሲሆን የሲንጋፖር፣ የጃፓንና ባለድርሻዎች ያሉበት ኩባንያ መሆኑን ተናግረዋል።**

**ኩባንያው ኤክስፖርት ተኮር እንደመሆኑ መጠን ከምክር ቤቱ ጋር በቅርበት መስራት እንደሚያስፈልገውም በውይይቱ ላይ ተነስቷል።**

**ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ሌሚ በበኩላቸው ኩባንያውን በሁሉም የአሰራር አግባቦች መሰረት ለማገዝና አብሮ ለመስራት ዝግጁ መሆኑን አረጋግጠዋል።**

**ኩባንያው ከመንግስት የአረንጓዴ ልማት ኢንሼቲቭ ጋር የተጣጣመ ንፁህ እና ዜሮ ብክለት ኢንቨስትምነት ላይ በመሰማራቱ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።**





## በዋና ፀሐፊው ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) የሚመራ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ልኡካን ከአሜሪካ ንግድ ምክር ቤት (አምቻም) ተጠባባቂ ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ሰላማዊት ባህሩ ጋር ውይይት አድርገዋል።

ውይይቱ በሁለቱ ምክር ቤቶች መካከል ያለውን ግንኙነት በማጠናከርna የጋራ ተልእኮን ለማሳካት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህም የንግዱ



ማህበረሰብ በንግዱ ዘርፍ በተወዳዳሪነት፣ በግልጸኝነት፣ በነጻ የንግድ እሴቶች እንዲመራ እና ግልጽ አጋርነት በመፍጠር ከአባሎቻቸው ዘንድ ዕድል፣ ንቅናቄ እና ትስስር እንዲፈጠር ማድረግ ነው።

በኢትዮጵያ እና በዩናይትድ ስቴትስ ያሉ የንግድ ድርጅቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግና ማራኪ እና ምቹ የንግድ ሁኔታ ለመፍጠር ሁለቱም ወገኖች በጋራ ለመስራት ተስማምተዋል።

የውይይቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ከዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ጋር የተጣጣመ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን፣ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የኢኮኖሚ ውህደት፣ ዲጂታል እና ፋይናንሺያል እውቀት፣ የምክር ቤቱ እና የአባል ምክር ቤቶቹ እና ማህበራት የዲጂታል ትስስር እና የግሉ ሴክተር ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ናቸው።

ሁለቱም ምክር ቤቶች ከፖሊሲ አውጪችና ከመንግስት ተቋማት ጋር የአድቮኬሲና የምርምር ስራዎችን በመስራት ምቹ የቢዝነስ ከባቢ እንዲፈጠር እንደሚሰሩ አረጋግጠዋል፡፡




በጋራ ጥረቶች፣ ምክር ቤቶች በንግድ ሥራ ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ ሕጎች እና ደንቦች ዙሪያ በምክክር በመስራት ፣ የአባላት ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ፣ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማስፋፋት እና ተወዳዳሪ የገበያ ቦታን ለማጎልበት እንደሚሰሩም ተጠቁሟል፡፡

የአሜሪካ ንግድ ምክር ቤት (አምቻም) ከ70 በላይ አባላት ያሉት ሲሆን አሜሪካዊ ድርጅት፣ በኢትዮጵያ የሚገኙ ቅርንጫፎች፣ ወኪሎች ወይም ተወካዮች፣ ከአሜሪካ እና ከኢትዮጵያ ጋር የንግድ ግንኙነት ያላቸው ድርጅቶች፣ ከኢትዮጵያ ኩባንያዎች ግለሰቦች ጋር የንግድ ወይም ሙያዊ ግንኙነት ያላቸው እና የአሜሪካ ኩባንያዎች ወኪል ሆነው ከሚሰሩ እና በኢትዮጵያ ኢንቬስትመንት ካላቸው በኢትዮጵያ የሚኖሩ የአሜሪካ ዜጎች ጋርም ግንኙነት አለው፡፡

**በአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ዉስጥ ምን አይነት ምርቶችን ይዘን ብንገባ ዉጤታማ ተወዳዳሪዎች ልንሆን እንችላለን የሚለዉን ሁሉም የንግዱ ማህበረሰብ ሊያስብ እንደሚገባ**





**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሐጅ አህመድ ሀሊፋ ተናገሩ።**

ፕሬዚዳንቱ ይህንን ያሉት በአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና መሠረታዊ ፅንሰ ሀሳቦች ዕድሎችና ስጋቶች ላይ ከክልሉ ለተዉጣጡ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አመራሮች የተሰጠዉ ስልጠና ሲጠናቀቅ ባስተላለፉት መልዕክት ነዉ።

በስልጠናዉ ግንዛቤ ማግኘታቸዉንና መነቃቃትን እንደፈጠረላቸዉ የስልጠናዉ ተሳታፊዎች ገልፀዉ መሰል ስልጠናዎች እስከ ታች ድረስ መዉረድ አለባቸዉ ብለዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ ለስልጠናዉ ተሳታፊዎች የምስክር ወረቀት ከሰጡ በኋላ ም/ቤታችን የአባላቱንና የመላዉ ንግድ ማህበረሰብ አቅምን ለመገንባት







የቢዝነስ አመራር አካዳሚ አቋቁሞ የተለያዩ ስልጠናዎችን እየሰጠ ስለሆነ የስልጠና ፍላጎቶቻችሁን በማሳወቅ ተጠቃሚ መሆን ትችላላችሁ ብለዋል።

## በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከGIZ-AU ጋር በመተባበር ለሁሉም ክልሎች እና አባል ምክር ቤቶች እየተሰጠ የሚገኘው  በአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና መሠረታዊ ፅንሰ ሀሳቦች ላይ የግንዛቤ መፍጠርያ ስልጠና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ለሚገኙ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች አመራሮች እና ነጋዴዎች ተሰጠ ::



**ስልጠናው የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አመራሮች፤ እየገባንበት ካለው አለም አቀፋዊና አህጉራዊ የንግድ ፉክክሮች አንፃር ለራሳቸዉ የተሻለ ግንዛቤ ኖሯቸዉ አባሎቻቸዉን ለፉክክሩ ማዘጋጀት እንዲችሉ ያደርጋል::**

**ሰብስብ አባፊራ አባጀቢር**

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት**

**Manni Maree Daldalaa fi Industirii Itiyoophiyaa GIZ-AU waliin ta'uun yaad-rimeewwan bu'uuraa Naannoo Daldala Walabaa Ardii Afrikaa irratti leenjii hubannoo uumuu naannolee fi manneen maree miseensota hundaaf kennaa jira. Leenjiin kun har'a hoggantootaa fi daldaltoota Mana Maree Daldalaa fi Industirii Naannoo Beenishaangul Gumuzitti kennamaa jira.**

**Leenjiin kun hoggantoonni Mana Maree Daldalaa fi Industirii dorgommii daldala addunyaa fi ardiilee nu mudachaa jiru caalaatti hubachuun miseensota isaanii dorgommii kanaaf akka qopheessan kan gargaaru ta'uu ibsameera.**

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በመተባበር የተቋቋመው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማሥተባበሪያ ክፍል በይፋ ስራ ጀመረ።**





የማስተባበሪያ ክፍሉ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እንዲሁም ከጅአይዜድ (GIZ) ጋር በመተባበር የተቋቋመው ነው።

ማስተባበሪያ ክፍሉ በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና መስሪያ ቤት ስራውን በጀመረበት ፕሮግራም ላይ የተገኙት የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ተሻለ በሬቻ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸው የክህሎት ማሣደግና የሥራ ፈጠራ በትኩረት የሚሠራባቸው መስኮች መሆኑንና አዲስ የተቋቋመው ክፍልም ለዚህ ትልቅ አጋጣሚ መሆኑን አንስተዋል። የመንግሥትና የግል ትብብር እጅግ አስፈላጊ መሆኑንም አስገንዝበዋል።

በፕሮግራሙ ላይ ሚኒስትር ዴኤታው ዶክተር ተሻለ በሬቻ፣ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቦርድ አባላት፣ የኢትዮጵያ አሠሪዎች ፌደሬሽን ፕሬዚዳንት ዶክተር ዳዊት ሞገስ፣ የጀአይዜድ




GIZ) STEP ማናጀር ሞሀመድ አሊ ካሃንና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ ( ተባባሪ ፕሮፌሠር) ማስተባበሪያ ክፍሉ በኢንዱስትሪውና በሥልጠና ተቋማት መካከል ያለውን የሠለጠነ የሠው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት የተሻለ፣ በፍላጎት ላይ የተመሠረተና ውጤታማ እንዲሆን ትልቅ ሚና እንደሚኖረው ገልጸዋል።

ሞሀመድ አሊ ካሃን በበኩላቸው በቴክኖክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ውጤት ለማምጣት የግሉ ዘርፍ ተሣትፎ በእጅጉ አሥፈላጊና ሊተካ የማይችል መሆኑን ገልጸው አሁን የተከፈተው የማሥተባበሪያ ክፍል ትልቅ ሚና እንደሚኖረው ጠቁመዋል። በቀጣይም ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን ሰለጠነና አስፈላጊውን ክህሎት ያለው የሰው ኃብት ለማፍራት ለሚደረገው ጥረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከምክር ቤቱ እንዲሁም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በትኩረት እንደሚሰራም በፕሮግራሙ በተካሄደው ውይይት ላይ ተነስቷል።

**የሴቶችን ቢዝነስና ያላቸውን ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ለማሳደግ ያለመ "Global Female Enterpreneurship Empowerment Programm- Ethiopia ወርክሾፕ" መሰጠት ተጀመረ።**

ፕሮግራሙ በቤጂንግ የውጭ ጥናት ዩኒቨርስቲ እና CCECC ኢትዮጵያ ኮንሥትራክሽን PLC ከኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት፣ ከኢትዮጵያ




ኢንቨሥትመንት ኮሚሽንና ከአዲስ ቻምበር ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው።

ለአስራ አራት ቀናት የሚቆየው ወርክሾፑ በቢዝነስ ሥትራቴጂያዊ እሣቤ፣ በቢዝነስ ሞዴል እንዲሁም ከቻይና ገበያ ጋር በተያያዘ ያሉ የቢዝነስ እድሎችን የሚዳስስ ነው።

በኢትዮጵያ የቻይና ኤምባሲ ሚኒሥትር ካውንሥለር ሊዩ ሺያጉዋንግ በፕሮግራሙ ላይ የሁለቱ ሃገራት ሁለንተናዊ ግንኙነት እየተጠናከረ መምጣቱን ገልጸው ይህ ወርክሾፕም የሴቶችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማሣደግና ዓለም አቀፍ የጾታ እኩልነትን ለማምጣት ያለመ የቻይና አንዱ የስትራቴጂ አካል ነው ብለዋል። በወርክሾፑ በተለያዩ የቢዝነስ መስኮች ላይ ተሰማሩ ሴት የቢዝነስ ባለቤቶች ተሳታፊ ናቸው።




**የዓለም አቀፍ ጥራት ኤክስፖ በጥራት መንደር ከህዳር 11 እስከ ህዳር 14/208 ዓ.ም በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትሩ ዶክተር ካሳሁን ጎፌ ተከፍቶ ተካሄደ ፡፡**






ይህ ዝግጅት የጥራት እውቅና ሰርቲፊኬት ያላቸው ተቋማት ብቻ የሚሳተፉበት መሆኑን የፕሮግራሙ አዘጋጅ የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ገልጿል፡፡ በዝግጅቱ ላይ ከተለያዩ ሀገሪቱ አካባቢዎች የጥራት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ያላቸው ተቋማት ብቻ እየተሳተፉ ሲሆን የሚካሄደውም "ጥራት፡-በተለየ እሳቤና ፈጠራ" በሚል መሪ ሐሳብ ነው፡፡ በጥራት መንደር የሚገኙ ተቋማት የትኞቹ ናቸው? አምስት ተቋማት ሲኖሩ አራቱ የጥራት 1. የቴክኖሎጂ ባለስልጣን 2. የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት 3. የስነ ልክ ኢንስቲትዩት 4. የደረጃዎች ኢንስቲትዩት 5. የአክሬዲቴሽን ኢንስቲትዩት ናቸው፡፡ የቴክኖሎጂ ባለስልጣን ተጠሪነቱ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሲሆን ቀሪዎቹ ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ነው፡፡

እነዚህ ተቋማት የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት በሚል የሚታወቁ ናቸው፡፡ ጥራት ያለው ምርትና አገልግሎት እንዲኖር ለማስቻል የሚሰሩ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ናቸው፡፡ የዚህ ኤክስፖ ዓላማም ህብረተሰቡ ጥራትን መሰረት አድርገው የሚሰሩ ተቋማትን እንዲያውቅና እንዲያበረታታ፣ ምርቶችን እንዲገዛ እንዲሁም የንግዱ ማኅበረሰብ ወደነዚህ ተቋማት በመምጣት የጥራት መመዘኛዎችን መሰረት





በማድረግ ማምረት እንዲችል ግንዛቤ መፍጠር ነው፡፡

የተቀመጡ የምርትና አገልግሎት መስፈርቶችን በማሟላትና በ International Organization for Standardization (ISO) መሰረት በማምረት ተወዳዳሪነትን ማሳደግና የተጠቃሚውን ደህንነት መጠበቅም ሌላው ዓላማ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የማርኬቲንግና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ተክኤ ብርሃነ አስመጭ እና ላኪዎች፣ አምራቾች እና ሌሎች ነጋዴዎች ለሚሰጧቸው አገልግሎቶች እና ለሚያቀርቧቸው ምርቶች የተቀመጡ መስፈርቶችን ሲያሟሉ የእውቅና ምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸውና በየጊዜው ፍተሻ እና ምዘና እንደሚደረግላቸው ገልጸዋል፡፡

የተስማሚነት ምዘና ድርጅትም ጥራትን ለማረጋገጥ በቀዳሚነት የፍተሽ ላብራቶሪ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን በባዮ ኬሚካልና በኤሌክትሮ ሜካኒካል 9 ላብራቶሪዎች አሉት፡፡ ሁለተኛው የኢንስፔክሽን አገልግሎት ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ የሲስተም ሰርቲፊኬሽን ነው፡፡

ይህም ከአይ ኤስኦ ስታንዳርድ አንጻር የጥራት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት መስጠት ማለት ነው፡፡ በየዓመቱ የሚካሄደው ይህ ዝግጅት የጥራት እውቅና ምስክር ወረቀት ያላቸውን ከሌላቸው ለመለየትና እውቅና ምስክር ወረቀት የሌላቸው ወደ ስታንዳርድ እንዲመጡና ማረጋገጫ እንዲኖራቸው ለማስገንዘብ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተጠቁሟል፡፡






# የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት







# የግሉ ዘርፍ ድምጽ!



**የንግድ ምክርቤቱ ራዕይ ፣ተልዕኮ ፣ እሴቶች እና ቀዳሚ ስትራቴጂካዊ አምዶች**

## ራዕይ

“በግሉ ዘርፍ የሚመራ ኢኮኖሚና አካታች ዕድገት በሁለት የስትራቴጂክ ዘመናት ውስጥ እውን ሆኖ ማየት”

## ተልዕኮ

“የኢትዮጵያን የግል ዘርፍ በመወከል፣ በመደገፍና ለመብትና ጥቅሙ አድቮኬት በማድረግ፤ ንግድን፣ ኢንቨስትመንትንና ፈጠራን በማስተዋወቅና በማበረታታት አካታች ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ብልፅግናን ማምጣት”

### ዕሴቶች

- ታማኝነት
- ሙያዊ ብቃት
- አባላት ተኮር ምላሽ ሰጪነት
- ትብብራዊ ጥምረት
- ግልፅነት
- ተጠያቂነት
- ማህበራዊ ኃላፊነት

### ቀዳሚ ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች (ስትራቴጂካዊ አምዶች)

1. አድቮኬሲና የፖሊሲ ተፅዕኖ
2. ጠንካራ የአባላት ተሳትፎና ድጋፍ
3. የሀብት ማሰባሰብና በአግባቡ መጠቀም
4. የአቅም ግንባታና ሥርዓት ማሻሻያ
5. ቴክኖሎጂን ማካተት እና ዲጂታል ሽግግር
6. ዘላቂነት ያለው ማኅበራዊ ኃላፊነት
7. ንግድና ኢንቨስትመንት ማስፋፋት
8. ሁሉን-አቀፍ ጉዳዮች (Cross-cutting issues)


ዋና አዘጋጅ፡-

ተሾመ ዋቅጂራ

ም/ዋና አዘጋጅ፡-

ደበበ አበበ

አዘጋጅ

ስማቸው ተበጀ

ፎቶግራፍ

ያለምፍሬ በቀለ





**The Ethiopian Chamber of Commerce and Secoral Associations (ECCSA)**

ስልክ: +251115514005

ፋክስ: + 251115517699

P. O. Box 517,

ኢ.ሜይል: info@ethiopianchamber.com

ድረ ገጽ: www.ethiopianchamber.com

ቴሌግራም t.me/ethiopiachamber

ትዊተር https://twitter.com/EthiopiaChamber

ፌስ ቡክ: https://www.facebook.com/EthiopianChamber

Youtube: https://www.youtube.com/channel/UCMEZ4TO8dQiIJvk2IQkTxhA

Linkedin(ሊንክዲን):https://www.linkedin.com/company/ethiopianchamber/in